# የቦረዳ ገዳመ ዮርዳኖስ ቅድስት ሥላሴ እና የቅዱስ ሚካኤል ገዳም የወፍጮ ኘሮጀክት አጭር የሥራ ሂደት ሪፖርት ቁጥር 3


የቦረዳ ገዳመ ዮርዳኖስ ቅድስት ሥላሴ ቤ/ክ

**የቤተክርስቲያኑ ስም ፡-**የቦረዳ ገዳመ ዮርዳኖስ ቅ/ሚካኤል እና ቅ/ሥላሴ ገዳም

**የሚገኝበት ቦታ ፡-** በሰሜን ኦሞ ሀ/ስብከት በቦረዳ ወረዳ ከአዲስ አበባ ወደ አርባ ምንጭ በሚወስደው መንገድ ከወላይታ 60 ኪ.ሚ ርቀት ከአዲስ አበባ ደግሞ 443 ኪ.ሜ ላይ ይገኛል፡፡

**የኘሮጀክቱ አስፈላጊነት፡-**የቦረዳ ገዳመ ዮርዳኖስ ገዳም ከተመሠረተ ጥቂት ዓመታት ቢሆንም ለመመሥረቱ ምክንያት የሆኑት በአካባቢው ያሉት ዋሻዎች እና በዋሻው ውስጥ የተገኙት ጽላቶች ጥንታዊና ታሪካዊ ይዘት ያላቸው በመሆኑ ታሪኩ ተጠብቆ ለትውልድ እንዲተላለፍ ለማድረግ በገዳሙ በአሁኑ ሰዓት ያሉትን መናንያ እና እየተሰጠ ያለው የንባብብና የቅዳሴ ትምህርት ለማጠናከር ገዳሙን ዘላቂነ የገቢ ምንጭ እንዲኖረው ማድረግ አስፈላጊ ስለሆነ የኘሮጀክት ጥናቱ ተዘጋጅቷል፡፡

**የኘሮጀክቱ ዓላማ ፡-**ገዳሙ በዘላቂነት ራሱን እንዲችልና አገልጋዮችን መናንያን በተመጻደሪያ እጦት ምክንያት ቦታውን ጥለው እንዲ ሰደዱ ማድረግ የአብነት ት/ቤቶቹን ለማጠናከር በአቅራቢያቸው ላሉ አብያተክርስቲያናት የአገልጋይ ካህናት ማፍሪያ እንዲሆን ማድረግ፣

**ሪፖርት የሚያጠቃልለው ጊዜ ፡-** ከግንቦት 2000 እስከ መስከረም 2001 ዓ.ም


በገዳሙ የሚገኙ የንባብ እና የቅዳሴ ተማሪዎች

**የኘሮጀክቱ ጠቅላላ በጀት፡-** 94,077 60/ዘጠና አራት ሺህ ሰባት ሰባት ብር ከሥልሳ ሳንቲም/

**የኘሮጀክቱን በጀት የሸፈነው አካል ፡-** 44,319.00 ሲዊዘር ላንድ ከሚገኙ ምእመናን

42,528.00 በማኅበረ ቅዱሳን አሜሪካ ማዕከል በኩል

7,230.00 ከገዳሙ የእንጨትና የጉልበት ዋጋ

**ገቢ የሆነው የገንዘብ መጠን ፡-** 86,847.60

**ኘሮጀክቱ ያለበት ሁኔታ** ፡ቀደም ሲል በቀረበው ሪፖርት መሠረት የወፍጮ ቤቱ ግንባታ የአጥር ሥራ አንድ ባለ 24 ፈረስ ጉልበት ሞተር እና ሁለት ባለ 50 እና ባለ 60 ቋት ወፍጮ እና ሌሎች ተጨማሪ ቁሳቁስ ተፈፅሞ ወደ ገዳሙ መላኩ ሪፖርት ተደርጓል፣

* የወፍጮ መትከል ፣
* የሠራተኛ ቅጥር የማከሄድ እና ሥራውን የማስጀመር ሥራ ተሠርቷል

ቀሪው ሥራ የፕሮጀክቱን ውጤታማነት መከታተል የኤሌክትሪክ መስመሩ እንደተዘረጋ ሞተሩን ወደዲናሞ መቀየር እና ከገዳሙ ጋር ርክክብ መፈፀም ሲሆን ይህም በእቅዱ መሠረት ርክክቡ በታሕሳስ 2001 ዓ.ም. ተፈፅሞ የማጠናቀቂያውን ሪፖርት ጥር 2001 ዓ.ም. የምንልክ መሆኑን እናሳውቃለን፡፡






በገዳሙ የወፍጮ ተከላ ሲካሄድ

## የሂሳብ ሪፖርት

* ለወፍጮ ቤት ግንባታ................ ............... 22,513.00
* ለወፍጮ እና ለሌሎች ቁሳቁስ ግዥ...............14,889.96
* ለናፍታ ሞተር ግዥ................................ ....... 13,913.04
* ለወፍጮ ማጓጓዧና ነዳጅ .............................. 4,700.00
* ለወፍጮ ማስተከያ ............... ..........................3,500.00
* ለፕሮጀክት ሥራ ማስፈጸሚያ /5% /........ 2,975.80
* ለፕሮጀክት ሥራ ማስኪያጃ/10 % /........ 5,951.60
* ጠቅላላ ድምር...................... **68,443.40**
* ቀሪ ገንዘብ ...................... 18,404.20 ወፍጮ ወደ ኤሌክትሪክ ሲቀየር ለዲናሞ መግዣ የሚውል

**ማኅበረ ቅዱሳን**
**የማኅበራዊ አገልግሎት እና ልማት ዋና ክፍል**
**የቅዱሳት መካናት ልማትና ተራድዖ ክፍለ**
**አድራሻ፡**
ስልክ፡ 251 11 1234531፣ 0911150478
ፖ.ሳ.ቁ. 80078 አ.አ ኢትዮጵያ